
ማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ
Mathiwos Wondu - YeEthiopia Cancer Society




ማቲዎስ ወንዱ
1991 - 1996 ዓ.ም

# ጋዜጣዊ መግለጫ

የማቲዎስ የ20 ዓመታት ጉዞ

# ጋዜጣዊ መግለጫ



## የማቲዎስ የ20 ዓመታት ጉዞ

መስከረም 13 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማቲዎስ ወንዱ ገና የሁለተኛ ዓመት ልደት ሻማውን በለኮሰ ከጥቂት ቀናት በኋላ በሉክሚያ (ALL-type Leukemia) በተባለ የደም ካንሰር ሕመም  ልጃቸውን በሞት ያጡት ወ/ሮ አምሳለ በየነና አቶ ወንዱ በቀለ እሱን የሚዘክርና በሕመሙ እየተሰቃዩ ያሉትን ለመርዳት የመሰረቱት  ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ  ብዙዎችን ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸውን እየደገፈ ይገኛል፡፡

ወላጆቹ ትንሹ ልጃቸውን በሕይወት ለማዳን ከሀገር ውስጥ ጀምሮ እስከ ባህር ማዶ የዘለቀ ጥረት ቢያደርጉም በሕይወት ሊተርፍላቸው አልቻለም፡፡ አባትና እናት ከመላው ዘመዶች ጋር በመሆን ያላቸውን ጥረት  አሟጠው ሕክምናው ይገኛል በተባለበት በሀገር ውስጥ፣ በደቡብ አፍሪካ ፣ በአውሮፓ፣ በሕንድና በአሜሪካ  ብዙ ሞክረዋል፡፡

በመጨረሻም አሜሪካን አገር ሕጻኑን ማቲዎስን ይዘው ለመሄድ ሲዘጋጁ መስከረም 13 ቀን 1996 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡



ምንም እንኳን ሀዘኑ ከባድ ቢሆንም የማቲዎስ ቤተሰቦች ሀዘኑን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር በተመሳሳይ ሁኔታ በካንሰር ህመም የተጠቁ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦችን ለመርዳትና ልጆቻቸውን መርዳት ሳይችሉ ሲቀሩ ከሚገቡበት የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመታደግ የሚሰራ ድርጅት ለማቋቋም ውሳኔ ላይ ደረሱ፡፡

እነሆ ውጥናቸው ሰምሮ ዛሬ በመላው ኢትዮጵያውያን በመልካም ምግባሩ የተከበረና በተዓማኒነቱ የሚታወቀውን ማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲን ሚያዚያ 9 ቀን 1996 ዓ.ም መሰረቱ፡፡

በዚህ በያዝነው ዓመትም 20ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ያከብራል፡፡

ድርጅቱ መጀመሪያ ትኩረቱን የህፃናት ካንሰር ላይ በማድረግ ተልዕኮዉን ጀመረ፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚደረገዉ የካንሰር ቁጥጥርና እርዳታ ለሚሹ የካንሰር ህሙማን ተገቢዉን ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

በትንሹ ማቲዎስ ስም የተጀመረው የሶሳይቲው ሥራ በእጅጉ አድጎ ዛሬ ለብዙ ሕሙማን መድህን ለመሆን ችሏል:: ሶሳይቲው በአሁኑ ሰዓት 1ሺህ 400 አባላት፣ 500 በጎ ፈቃደኞች ፣ 30 ቋሚ ሰራተኞችን ይዞ ትልቅ ድርጅት ለመሆን በቅቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በቁጥር ስምንት ፕሮጀክቶች ይዞ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በቁጥር 152 የሚደርሱ የካንሰር ህሙማንንና ቤተሰቦቻቸውን ትርጉም ባለው ሁኔታ ይደግፋል፡፡

በተጨማሪም ሕክምና በሚሰጥበት የጤና ተቋማት የማይገኙ የመድኃኒት፣ የላቦራቶሪና ሕክምና ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡ ለሕሙማንና ቤተሰቦች ለትራንስፖርት የሚሆን ሙሉ ወጪ በየወሩ ይሸፍናል፡፡

ሕክምናቸውን እየተከታተሉ ለሚማሩ ሕጻናት ታካሚዎች ድርጅቱ ሙሉ የትምህርት ወጪያቸውን ይሸፍናል፡፡ ከክልሎች በመምጣት በአዲስ አበባ ሕክምናቸውን ለሚከታተሉ ሕሙማን 24 አልጋ ባሉት ማቆያ ማዕከሉ የመጠለያና የምግብ አገልግሎት በነፃ ይሰጣል፡፡ እነዚህ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው የሳይኮ ሶሻል አገልግሎትም ያገኛሉ፡፡

ለካንሰር ሕሙማን ሰፊ ድጋፍ እያደረገ ያለው ይህ ስመ ጥሩ ድርጅት በዓለም አቀፍ ደረጃ አምስት፣ በአገር ውስጥ  ሁለት ብሔራዊ በጠቅላላው ሰባት ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡

ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ በውስን አቅሙ በኢትዮጵያ እያደገ የመጣውን የካንሰር ህመም ጫናን ለመቋቋም በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡



መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለይ ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች ከዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ለጋሾች ድጋፍ ውጪ ስራቸውን ዳር ማድረስ አይችሉም፡፡ የተለያዩ ሪፖርቶች ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ችግር ኢትዮጵያን በየዓመቱ 31 ቢሊዮን ብር እያስወጣት እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ይህም በየዓመቱ ሲሰላ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ 1.8 በመቶ ይደርሳል፡፡

በመስኩ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ችግር እየጨመረ የመጣ የጤና ብቻ ሳይሆን የልማትም እንቅፋት እንደሆነ ነው፡፡ ይህን የጤና ችግር ከወዲሁ ለመቅረፍ ለጋሾች ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ባለው ውሱን በጀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ስርጭት ለመቀልበስ በተለይ በካንሰር ሕመም ዙሪያ እየሰራ ይገኛል፡፡

## በሶሳይቲው የሚደገፉ ፕሮጀክቶች

## 1.በጤና ሚኒስቴር የተጀመሩ እና የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች፡

- **ብሔራዊ የካንሰር መቆጣጠሪያ ዕቅድ** (NCCP):

  ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ፒንክ ሪበን ሬድ ሪበንና ጂ.ኤስ.ኬ ከተባሉ ድርጅቶች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የጤና ሚኒስቴርን የብሔራዊ የካንሰር መቆጣጠሪያ ዕቅድ እንዲያዘጋጅና እንዲተገብር አድርጓል፡፡ ይህም የካንሰር መቆጣጠሪያ ፕላን በሀገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያውና በአፍሪካ አህጉርም በዓይነቱ በጀት ከተመደበላቸው ጥቂት ዕቅዶች አንዱ ነው፡፡

- **ብሔራዊ የህጻናትና የአዋቂዎች የካንሰር መቆጣጠሪያ ዕቅድ**( NCACCP)፡

  ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ከአሜሪካ የሕጻናት አካዳሚ ከሚባል ግብረ ሰናይ ድርጅት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የጤና ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ ያዘጋጀውን የሕጻናትና አዋቂዎችን የካንሰር መቆጣጠሪያ ዕቅድ ሰነድ በማዘጋጀት እንዲተገበር አድርጓል፡፡ ይህ መቆጣጠሪያ ሰነድ በሀገራችን ሲዘጋጅ የመጀመሪያው ሀገር አቀፍ ሰነድ ነው፡፡

- **ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችና ድንገተኛ ጉዳቶች ሪፖርት**( NCDI Report):

    ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ኖርዌይ ከሚገኘው የበርገን ዩኒቨርስቲ፣ ሀርቫርድ ዩኒቨርስቲና ኤን.ሲ.ዲ.አይ ፖቨርቲ ኔት ወርክ ከተባሉ መቀመጫቸውን አሜሪካ ካደረጉ ድርጅቶች ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ተላላፊ ያልሆኑ ድንገተኛ ጉዳቶች ሪፖርት ከጤና ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ ሪፖርት እንዲያወጣ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ይህም ሪፖርት በዓይነቱ የመጀመሪያው ነው፡፡

## 2.**በኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን**/EFDA/ **የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች**:

- **ካምፔይን ፎር ቶባኮ ፍሪ ኪድስ ፡**

  ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ካምፔይን ፎር ቶባኮ ፍሪ ኪድስ (CTFK)ና አፍሪካ ካፓሲቲ ቢዩልዲንግ (ACBF) በተገኘ የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ  በኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን በኩል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በማስረዳትና በማሳወቅ በትምባሆና በአልኮል መጠጥ ቁጥጥር እንዲደረግና በትምባሆና በአልኮል መጠጥ ላይ ጠንካራ ህግ እንዲወጣ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ይህም ህግ በጠንካራነቱ ከአፍሪካ አህጉር በግንባር ቀደም የተቀመጠ ህግ በመሆን በአርአያነቱ እየተጠቀሰ ይገኛል፡፡

## 3. **ዩኒቨርሳል የጤና ሽፋን እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሪፖርት፡**

ከዓለም አቀፉ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ጥምረት (NCDA) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የኢትዮጵያን ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ጥምረት ፕሮጀክትን ለመደገፍ ረድቷል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዋና ግቡ በተቀናጀ ጥረት ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመቆጣጠር ነው፡፡ ይህም በሀገሪቱ በህመሙ የመሞት አጋጣሚና የሚመጣውን ጉዳት ለመቀነስ ይረዳል፡፡ ሶሳይቲው የዩኒቨርሳል የጤና ሽፋንና በኢትዮጵያ በአይነቱ የመጀመሪያው የሆነውን ሪፖርትም ይፋ ለማድረግ ችሏል፡፡

ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ በማህበረሰባችን አኗኗር ውስጥ ትልቅ ልዩነት በማምጣት ላይ ያለና በምሳሌነት የሚጠቀስ ድርጅት ነው። በዚህም በሀገር ውስጥ የሰራው ግዙፍና ምሳሌነት ያለው ሥራው በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ዕውቅናን አስገኝቶለታል፡፡

- **Enabler of Vision Award (የኢነብለር ኦፍ ቪዥን ሽልማት):** ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ይህን ሽልማት ያገኘው እ.ኤ.አ 2017 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (በተ.መ.ድ) በዓለም አቀፉ የስርዓተ ጾታና ቀጣይነት ያለው የልማት ዕቅዶች ጉባዔ ኒውዮርክ ላይ ሲካሄድ የተሰጠ ነው፡፡

- **ለማህበረሰብ የተደረገ ከፍተኛ የማህበራዊ አገልግሎት ሽልማት :** ይህ ሽልማት የተገኘው ፒፕል ቱ ፕፕል ከተሰኘ በሰሜን አሜሪካ በሚኖሩ ቁጥራቸው አምስት ሺህ የሚደርሱ ዶክተሮችና ኢንጅነሮችን ኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራ ካቀፈ ማህበር ነው፡፡

- **የሥራ አስፈጻሚ ሽልማት(CEO Award):** ይህ ሽልማት ከ1,200 በላይ አባላት ባሉት ከዓለም አቀፉ የጸረ ካንሰር ሕብረት (International Union Against Cancer) የተገኘ ነው፡፡ በዚህም የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንዱ በቀለ ከመላው ዓለም ለሽልማቱ ከታጩ ሦስት ኃላፊዎች አንዱና ከአፍሪካ ብቸኛው ናቸው፡፡

- **Warrior Against Cancer:** ይህ ሽልማት BMSF የተባለ ድርጅት ፕሬዝዳንት ከሆኑት ዶ/ር ጆን ዳሞንቲ የተበረከተ ሲሆን ድርጅታቸው 20ኛውን የምስረታ በዓሉን በደርባን -ደቡብ አፍሪካ ሲያከብር እ.ኤ.አ በ2019 የተገኘ ነው፡፡

- **የዓለም ሲጋራ የማይጨስበት ቀን ሽልማት:** የማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ወንዱ በቀለ ለዚህ ሽልማት ከአፍሪካ አህጉር ከተመረጡት ስድስት ተሸላሚዎች አንዱ ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ 2020 ከዓለም ጤና ድርጅት የተላከውን የዓለም ሲጋራ የማይጨስበት ቀን ሽልማት፣ ሰርተፊኬት እና ሜዳሊያ አቶ ወንዱ በቀለ፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የዓለም ጤና ድርጅትና የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ኃላፊዎች በተገኙበት ተቀብለዋል፡፡

- **የላቀ የሥራ አፈጻጸም ሽልማት(Center of Excellence):** ይህ ሽልማት የተሰጠው ቴክኒካዊ መሰረትን ድጋፍ አድርጎ የፋይናንስ አስተዳደርን፣ ፕሮጀክት አስተዳደርን፣ ድርጅታዊ መዋቅርን ለማሻሻል፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም የላቀ ከፍተኛ አቅም ያለውና ትልልቅ ፕሮጀክቶችን የመፈጸም አቅም ያለው በማለት ለማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ከአሜሪካው የዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ኤጀንሲ (USAID) የኤል.ሲ.ዲ ቡድን ከፍተኛ የምስክር ወረቀት አግኝቷል፡፡

- **የላቀ ስራ አፈጻጸም ምስክር ወረቀት:** ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሳንባና የጽኑ ሕሙማን ሕክምና መርሐግብር ላደረገው አስተዋጽኦ ከኢትዮጵያ ቶራሲክ ሕክምና ማህበር የላቀ አፈጻጸም የምስክር ወረቀት አግኝቷል፡፡

- **የ50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዮ ሽልማት:** ይህ ሽልማት ለማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የተሰጠው ከክርስቲያን በጎ-አድራጎትና ልማት ማህበራት ሕብረት ነው፡፡ ምክንያቱም ጥምረቱ የ50ኛ ዓመት በዓሉን ሲያከብር የማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ትምባሆን ለመቆጣጠር ላደረገው መልካም ሥራ በጥምረቱ ከተመረጡ አምስት ምርጥ ሥራዎች አንዱ ተደርጎ ለሌሎች ምርጥ ተሞክሮ ያለው በማለት ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡





# በመተግበር ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች:

- **የሕጻናት ካንሰር ሚቲጌሽን ፕሮጀክት፡**

  ይህ ለማቲዎስ ወንዱ የመጀመሪያው የሆነው ፕሮጀክት በአብዛኛው በሀገር ውስጥ ለጋሾች ድጋፍ የሚተገበር ነው፡፡ ከ2 ሺህ በላይ የሚሆኑ የካንሠር ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው  በዚህ መርሐግብር ተረድተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በቁጥር ከ154 በላይ የሚደርሱ ሕሙማንና ረዳቶቻቸው በመደገፍ ላይ ናቸው፡፡ የሳይኮ ሶሻል ድጋፍ ወጪ በመጨመሩ በሀገር ውስጥ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮጀክቱ ዳር እንዲደርስ እየተሰራ ነው፡፡

- **የትምባሆ ማሰጠንቀቂያ ምልክቶች ፕሮጀክት፡**

  ይህ ፕሮጀክት በሲጋራ ማሸጊያዎች፣ የሚደረጉ የስዕላዊ ማስጠንቀቂያዎችና በመላ ሀገሪቱ ከሲጋራ ነጻ የሆኑ አካባቢዎችን ለማስፋፋት ሕግና መመሪያን ለመተግበር እንዲቻል በመስራት ላይ ነው፡፡

- **ከትምባሆ ነጻ አካባቢን የማስፋት ፕሮጀክት፡**

  ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ የሥራ ተቋማትና የማህበረሰቡን መኖሪያ አካባቢ ከትምባሆ ነጻ ለማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራትን ይመለከታል፡፡ በተጨማሪም ሆቴሎችና መዝናኛ ስፍራዎች ሙሉ ለሙሉ ከትምባሆ ነጻ ለማድረግ የሚደረገውን እንቅስቃሴን ይጨምራል፡፡

- **የሳንባ ካንሰር ምርመራና ቁጥጥር ፕሮጀክት፡**

  የማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ የሳንባ ካንሰር ፕሮጀክት ላለፉት ሦስት ዓመታት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ክልል፣ በአፋር ክልልና አዲስ አበባ ከተማ ተጀምሯል፡፡ ቢ.ኤም.ኤስ.ኤፍ ከተባለ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ  በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚገኙትን በቁጥር 15 የሚደርሱ የደረት (Chest) ሕክምና ክፍሎች በማደስ እንዲሁም ለሕክምና ክፍሉ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነውን ብሮኖስኮፒና ኢበስ (በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው) የተባሉ መሳሪያዎችን በ6 .5 ሚሊዮን ብር ገዝቶ አስረክቧል፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የሳንባ ህክምናንና ሌሎች ህክምናዎችን ለማከም አስችለዋል፡፡

- **ፔን ፕላስ ፕሮጀክት** (PEN-Plus Project):

  ይህ ፕሮጀክት ከኤን.ሲ.ዲ.አይ ፖቨርቲ ኔት ወርክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ  በኢትዮጵያ የማይተላለፉ በሽታዎች የሚያስከትሏቸው ሕመሞችን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ለማከም የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠርን ይመለከታል፡፡ ፕሮጀክቱ ዋና ዓላማው በላቀ ሁኔታ የደም ግፊትን፣ የልብ ድካምን፣ በልብ ቧንቧ እና በስትሮክ የሚመጣ የልብ የጤና ችግር ፣ ከመተንፈሻ አካላት ጋር ተያይዞ  በሳንባ ላይ የሚከሰት ጉዳትን በመቀነስ  ማከም ነው፡፡

  በዚህ ረገድ የፔን ፕላስ ክሊኒኮች በሙከጡሪ (ኦሮሚያ)ና በአዲስ ዘመን (አማራ) አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ወደፊትም እነዚህን ክሊኒኮች በመላው ሀገሪቱ ለማስፋፋት ዕቅድ ተይዟል፡፡ ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው እና ብቸኛው ነው፡፡

- **የኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ  በሽታዎች መከላከል ጥምረት አዲቮኬሲን ማጠናከር፡**

  የዚህ ፕሮጀክት አብይ አላማ ንቅናቄ በመፍጠር በሽታን መከላከልና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞችን ለመቆጣጠር፣ በህመሙ ሳቢያ የሚከሰትን ሞትና ጉዳትን ለማስቀረት ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ጊዜ የተጠናቀቀ  ቢሆንም ቀጣይነት እንዲኖረው እየተሰራ ይገኛል፡፡

- **የኢትዮጵያ የምግብ ፖሊሲን መደገፍ፡**

  ኢትዮጵያ ዋና የምግብ ፖሊሲ እንዲኖራትና ጤናማ የአመጋገብ ስርዓትን እንድትከተል ስርዓት መዘርጋት የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ ነው፡፡ ይህም ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው፡፡

- **የሳንባ ካንሰር ጤና ኢኒሼቲቭ፡**

  የማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ላንግ አምብሽን ጥምረት ኢኒሼቲቭ በሳንባ ካንሠር ኬር (ILC2) መርሐግብር  አባል ሆኗል፡፡ የላንግ አምብሽን ጥምረት አኒሼቲቭ በካንሠር ሕክምና ዙሪያ በማህበረሰብ ውስጥ ለሚከናወኑ ስራዎች የዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠትና ለማሻሻል ይሰራል፡፡

  በዚህ ረገድ የማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ ከአጋሮቹ ጋር ፕሮጀክቱን ለመተግበር ተፈራርሞ በሥራ ላይ በማዋል ላይ ይገኛል፡፡

- - -









ማቲዎስ ወንዱ

1991 - 1996 ዓ.ም

ማቲዎስ ወንዱ - የኢትዮጵያ ካንሠር ሶሳይቲ
Mathiwos Wondu - YeEthiopia Cancer Society

MWECS Head Office & Phangisile Psychosocial Support Center
Togo Street, Addis Ababa, Ethiopia
+251 118 12 2838 Email: contact@mathiwos.org P.O.Box No: 80571
www.mathiwos.org